# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

**የልጆች አግልግሎት ቀን**

በOctober 27 በሚኖረው የሕሁድ አገልግሎት ልጆቻችን አዋቂዎችን የሚያገለግሉበት እለት ነው። በዚህ እለት ስለሚኖረው ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ እናሳስባለን። የተለየ ግሩም ግዜ ስለሚኖረን በዚህ ፕሮግራም ሁላችንም እንድንካፍለ እናበረታታለን።

**እርስ በርስ እንተያይ**

ባለፈው ሳምንት የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።" (ዮሐ. 14:15-16)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**September 22, 2019** | **መስከረም 11፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** ............................ | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| **አምልኮ**.......................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............. | ወንድም ተረፈ አንሼቦ |
| **ልጆችን ለጌታ ማስረከብ** ____ | ወንድም ተረፈ አንሼቦ |
| **ቃል** ................................ | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| **ማጠቃለያ** ...................... | ፕሮግራም መሪ |

“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።” (ዮሐ. 14:26)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

### የመንፈስ ቅዱስ የስራ ዘመን ነው።

ባለፈው ሳምንት በነበረን ኮንፈራንስ ላይ እግዚአብሔር “ይህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ የስራ ዘመን” እንደሆነ ተናግሮናል። መንፈሳችንንም በዚህ ዙሪያ ሲያነቃቃው ነበር። እውነት ነው ይህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው። አሁን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሆኖ አብና ወልድን እያከበረ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው ትልቁ ተስፋ መንፈስ ቅዱስ ነው። ጌታ እንዲህ አላቸው፡ “ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።” (ዮሐ. 14፡ 15-17) በዚህ ቃል ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምንማራቸው በርካታ ነጥቦች አሉ።

በመጀምሪያ መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከኛ ጋር ነው። ጌታ ኢየሱስ በምድር ለተወሰኑ አመታት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተመላልሷል። እስከ መስቀል ሞት ድረስ በመታዘዝም የአባቱን ፈቃድ ፈጽሞ ለደህንነታችን ቤዛ ሆኗል። አሁን ደግሞ በክብር ከፍ ከፍ ብሎ በአብ ቀኝ አለ። እኛንም የልጅነትን ስልጣን ሰጥቶን ከርሱ ጋር በአብ ቀኝ በከበረ ስፍራ አስቀምጦናል። ነገር ግን አሁን ጌታችን ዳግመኛ መጥቶ ቤተ ክርስቲያንን እስኪወስዳት ድረስ ከኛ ጋር ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ከኛ ጋራ ነው። አሁን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይሰራል። ሙሽራይቱን ለክርስቶስ አያዘጋጀ አብሯት እስከ መጨረሻው ይቆያል።

ሁለተኛው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ እንደ ጌታ ኢየሱስ ያለ ሌላ አጽናኝ መሆኑ ነው። “አጽናኝ” -- Comforter -- ፓራቅሊጦስ-- Counselor የሚለው ቃል “ረዳት፣ በሁሉም ጉዳይ የምንፈልገው፣ የምናማክረው፣ የምንጠይቀው” ማለት። ጌታ በምድር በነበረበት ጊዜ የቃሉን ሚስጠር እየገለጠ፣ በአጋንንት የተያዙትን ነጻ እያወጣ፣ ድዊያንን እየፈወሰ፣ የመንግስቱን ወንጌል እየሰበከ በአጠቃላይ የአባቱን የአብን ፍቃድ እያደረገ ተመላልሷል። ሐዋሪያቱና ደቀ መዛሙርቱ በሁሉ ነገር ዘወር ብለው ይመለከቱ የነበረው ጌታን ነው። እምነታቸው ሲናወጥ ወደ እርሱ ተመልክተው ይጽናናሉ። ጥያቄ የሆነባቸውን ነገር ሁሉ ወደ እርሱ ያቀርባሉ። መንፈስ ቅዱስ “ሌላ አጽናኝ” ሆኖ ይህንን ስራ ለመቀጠል ነው የመጣው። ሐዋሪያቱ በነገር ሁሉ ወደ ጌታ ዘወር ይሉ እንደነበር እኛም በነገር ሁሉ ወደ መንፈስ ቅዱስ ዘወር እንል ዘንድ ያስፈልገናል።

ሶስተኛው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል። (ዮሐ. 16:13) መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ማንነት፣ አዳኝነትና ትንሳኤ እየመሰከረ ሰዎችን እውነት ወደ ሆነው ክርስቶስ ይመራል። የግዚአብሔርን እውነት በአማኝ ልብ በማብራት የቃሉን መገለጥ ይሰጣል። መንፈፈስ ቅዱስ ባለበት እውነትና ብርሃን ስለሚገለጥ ሰዎች በቃሉ ኃይል እየተነኩ ለመዳን ምን እናድርግ እያሉ ወደ እውነት ምንገድ ይመጣሉ።

የመጨረሻው በዚህ ክፍል ያለው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ ከኛ ጋር እና በኛ ውስጥ መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስን አለም ሊያውቀው አይችልም። እኛ ግን እናውቀዋለን። በውስጣችን ነው፤ አብሮን ነው። እኛ የእርሱ መቅደሶች ነን። በምንገባበትና በምንወጣበት ሁሉ ይህንን የክብር መንፈስ ይዘን እንንቀሳቀሳለን። ይህ የክብር መንፈስ አምላክ ነው፣ ፈጣሪ ነው፣ ህይወት የሚሰጥ ነው፣ ቅርጽ ለጠፋበት አለም ቅርጽ የሚሰጥ ነው፣ በጨለማ ውስጥ ብርሃን ነው፣ ለአገልብሎታችን ደግሞ ኃይል የሚሰጠን ነው፣ በድንቅና በታምራትም ስለ ኢየሱስ ትንሳኤ የሚመሰክር ነው። ማን በውስጣችን እንዳለ እናስተውል ይሆን? ለጌታ ለመንፈስ ቅዱስ እውቅና እየሰጠን እንመላለስ።